# ጄኔራል ፃድቃን፣ ኢሕአዴግና የሰሜን አፍሪካ አብዮት

## እስክንድር ነጋ

## ከአዲስ አበባ

ጥድፊያ፣ ጥድፊያ፣ ጥድፊያ:: ሰዓቱ እየከፈነ ነው:: ገና መጣጥፉ አላለቀም፤ ይቀረዋል:: መፃፍ.... ማረም... መደለዝ... እንደገና መፃፍ... ማስተካከል.. ምን ማለቂያ አለው?... ሁለት ሰዓታት ይቀራሉ... ለመጨረሻዋ ቡና ጊዜ አለ:: እፎይ!....

የዓርብ የግማሽ ቀን ውሎ ይሄን ይመስላል.... ለእኔ ለፀሐፊው:: በዋሽንግተን ካለው ግዙፉ የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ ጋር የዓርብ ማለዳ ቀጠሮ ከያዝኹኝ ይኸው ሰነባብቻኹ:: ይቺ ቀጠሮ እንዳትፋለስ ነው ጥድፊያው:: ሌላው ዲያስፖራ እንኳን በሚመቸው ሰዓት ነው የሚያገኘኝ::

ኢሜሌን ዘግቼ ብድግ አልኹ:: ኢሜል የሚከፈተው በመከራ፣ የሚዘጋው በመከራ:: ፈጣን ኢንተርኔት በሰሜን አፍሪካ አብዮት ወልዷል:: አብዮትን ዘወትር እየፈራ የሚኖረው ብልጣ ብልጡ ኢህአዴግ፣ ኢንተርኔቱን ትቶ ከፍጥነቱ ጋር ተናንቋል:: «የቸገረው እርጉዝ ያገባል» እንዳሉት፣ የአብዮትን «ምንጭ» ማድረቁ ነው::

«አንድ ሰዓት ከሰባት ደቂቃ» አለችኝ ልጅቷ በትህትና:: ድንግጥ አልኹኝ:: ይሄን ያህል የተቀጠምኹ አልመሰለኝም:: ሰዓቱ እውነትም ክንፍ አውጥቷል::

አቀርቅሬ ከኢንተርኔት ካፌዋ በፍጥነት ለቀቁ ወጣኹ:: መልስ እንኳን አልጠየኹም:: ወደ ቀኝ ታጥፌ ረጅሙን ኮሪደር ሸመጠጥኹት... የሕንፃው ዋና በር ላይ ደርሻለኹ.... አሁን የቀረኝ ደረጃውን መውረድ ብቻ ነው... እንዳቀረቀርኹኝ ነው...

«እሱ ነው»... የሚሉ ቃላት ሲያቃጭሉ ቀና አልኹ::

ከሁለት የፌዴራል ፖሊስ አባላትና በሲቪል ልብስ ካሸበረቀ የደህንነት አባል ጋር ደረጃው ላይ ተገጣጠምን:: ፊት ለፊቴ ያለው ፌዴራል ፖሊስ የመገናኛ ሬዲዮ ይዟል:: ከኋላው ክላሽንኮቭ በተጠንቀቅ የያዘ ግዙፍ ፖሊስ አስከትሏል:: የሽሚዙ እጅ ተጠቅልሏል:: ጡንቻዎቹ ያባበጡ ናቸው:: ክላሹን እንደስንጥር አንጠልጥሏታል:: እኔም... እሱም... ሳናስበው ዓይናችን ገጠመ:: ወጣት ነው:: ቢበዛ ሃያ አመታት አያልፈውም:: ግር ብሎታል፤ ተጨንቋል:: ፊፀሞ «ወንጀለኛ» ለመያዝ የመጣ አይመስልም::

«ይፈለጋሉ...» አለኝ፤ መገናኛ የያዘው ፖሊስ ጎርነር ባለ ድምፅ:: የዚህኛው ፖሊስ እጀታ አልተጠቀለለም:: ግርግር እንዳይፈጠር እየተጠነቀቀ ይመስላል::

«ይቻላል...» አልኹኝ፤ ቆም ብዬ::

ሳላውቀው ፈገግ አልኹኝ:: ለስምንተኛ ጊዜ  ወደ እስር ቤት ላመራ ነው:: የሕፃኑ ልጄ ገፅታ እንደ ድንገት ብልጭ ሲልብኝ ግን፣ የፊቴ ገፅታ ሲለዋወጥ ተሰማኝ:: ሐሞቴ የፈሰሰ መሰለኝ:: አዲስ ክስተት፣ አዲስ ስሜት:: ሰባቴ ስታሰር ልጅ አልነበረኝም::

«ይቀጥሉ...» አለኝ፤ መገናኛ የያዘው ፖሊስ ከኋላዬ ሆኖ::

የደረጃውን ቁልቁል ዘለቅኹት:: ፊት ክላሽ የያዘው ፖሊስ አለ:: መሐል አስፋልት ላይ ወደቆመችው ክፍት ላንድክሩዘር መራኝ:: እርምጃው ፍጥነት አለው:: ሰው እየተሰበሰበ ነው:: አካባቢውን በፍጥነት መለቀቅ ፈልገዋል:: የላንድክሩዘሩ ጀርባ ክፍት ነው:: ሶስት ፖሊሶች ክላሽ ታጥቀው በንቃት ዓይናቸውን ተክለውብኛል:: ከመኪናዋ ላይ በፍጥነት ለመውረድ የተዘጋጁ ይመስላሉ:: ገና ለጋ ወጣቶች ናቸው:: ከሃያ እና ከሃያ አንድ አያልፉም::

ላንድክሩዘሯ መሐል አስፋልት ይዛ በመቆሟ የመኪና መተላለፊያ ተዘግቷል:: መኪናዎች ከኋላዋ ተደርድረዋል:: አላፊ አግዳሚውም እንቅስቃሴውን ገትቷል:: ቆሞ ትዕይንቱን በጉጉት ይከታተላል:: የአካባቢው ትኩረት ሁሉ በእኔ ላይ አርፏል::

«ይግቡ...» አለኝ፤ መገናኛ የያዘወ ፖሊስ የላንድክሩዘሩን በር እየከፈተ::

የፌዴራል ፖሊስ የደንብ ልብስ የለበሰው አሽከርካሪ ብቻ ዞር ብሎ አልተመለከተኝም:: ፊቱን ኩምትር አድርጎ አካባቢውን ለቆ ለማፈትለክ ተቻኩሏል:: ቤንዚኑን ቶሎ ቶሎ ረገጥ... ረገጥ ያደርጋል:: ተንሸራትቼ አጠገቡ ቁጭ አልኹኝ:: መገናኛ የያዘው ፖሊስ ጎኔ ተቀመጠ:: በሩን በአግባቡ እንኳን ሳይዘጋ ላንድክሩዘሯ ወደፊት ተወረወረች::

ጉዞ ወደ ደጎል አደባባይ አቅጣጫ:: ላንድክሩዘሯ በፍጥነት ነው የምትነጉደው:: ጋቢና ውስጥ ፀጥታ ሰፍኗል:: መገናኛ የያዘው ፖሊስ መያዜን አበሰረ:: የሾፌሩ ፊት አሁንም አልተፈታም::

«ወደ ሜክሲኮ...» አለ፤ መገናኛ የያዘው ፖሊስ ደጎል አደባባይ ስንደርስ::

ፊፅሞ ያልጠበኹት ነገር:: አቅጣጫችን «ሁለተኛ ቤቴ» ወደምለው ማዕከላዊ ምርመራ መስሎኝ ነበር:: ሹፌሩ ግን ጭራሽ ፍጥነት ጨምሮ ወደ እየሩሳሌም ሕንፃ አቅጣጫ በረረ::

አሮጌ ፖስታን አልፈን ቸርቸርን ተያያዝነው... የላንድክሩዘሩ ፍጥነት እየጨመረ ነው... ቴዎድሮስ አደባባይ... ጥቁርአንበሳ... ብሔራዊ ባንክ... ዋቢሸበሌ... ሜክሲኮ አደባባይ... ወደ ሳር ቤት በሚወስደው መንገድ በኩል የፌዴራል ፖሊስ ዋና መሥሪያ ቤት የመኪና መግቢያ ላይ ላንድክሩዘሯ ቆመች:: ግልግል:: ክላሽ የያዘ ፌዴራል ፖሊስ ተጠጋን:: መገናኛ የያዘው ፖሊስ አንገቱን በመስኮት አወጣ::

«ታዲያስ?...» አለው::

ፖሊሱ መለስ አለ:: በሩ ተከፈተ:: አሁን በዝግታ ወደ ግቢው ዘለቅን:: ፀጥ ረጭ ያለ ግቢ ነው:: የሕንፃው ጀርባ ነው:: ላንድ ክሩዘሯ በሕንፃው የኋላ መግቢያ በር ላይ ቆመች:: መገናኛ የያዘው ፖሊስ ወረደ::

«ልውረድ እንዴ?...»

«አዎ!...» አለኝ::

ፊት ፊት እየመራ ወደ ሕንፃው መግቢያ አመራን:: በሩ ላይ ፖሊሶች ተቀምጠዋል:: እነዚህ ግን ክላሽ አልያዙም::

«ኮሚሽነር ጋር ነው...» አላቸው፤ ከጀርባው የሽጎጣትን ሽጉጥ እያወጣ::

አንዱ ፖሊስ ሽጉጡን ተቀበለው:: በማንነቴ ግራ እንደተጋባ በገፅታው ላይ ይነበባል::

«ኮሚሽነር ፈልጎት ነው...»

ፖሊሱ አንገቱን ነቀነቀ::

«እንሂድ...» አለኝ፤ መገናኛ የያዘው ፖሊስ ፊት ለፊት እየመራ::

ኮስተር.... ኮስተር ያሉ የፌዴራል ፖሊስ ባለስልጣናት ውር... ውር... ይላሉ:: በስራ የተወጠሩ ይመስላሉ:: አንዳንዶቹ «ማንነው?» በሚል ስሜት እየቃኙኝ ያልፋሉ:: እንግዳ የሚያዘወትረው ሕንፃ አይደለም::

ሲቪል የለበሰ ሰው ተቀበለን:: ሰላምታ አልሰጠንም::

«ወደዚህ...» በማለት ወደ አንዲት ትንሽ ቢሮ ይዞን ገባ:: ሁለት ትላልቅ ጠረጴዎች ክፍሏን አጣበዋታል::

«ኪስህ ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ አውጣ:: ኮሚሽነሩ ጋር ምንም ይዞ መግባት አይቻልም...» አለኝ፤ ለስለስ ባለ ድምፅ:: ገፅታውም ሆነ ድምፁ ከፖሊስ ይልቅ ወደ ምሁር ያጋደለ ነው::

«ወረቀቶች ነው የያዝኹት...» አልኹኝ፤ እጄ ላይ የያዝኳቸውን በርካታ ወረቀቶች እያሳየኹት:: ወረቀቶቹን ተቀበለኝ:: መጣጥፌ ፖሊስ እጅ ገባ::

«ኪስህ ውስጥስ?...»

«ከኋላ ኪሴ ውስጥ ወረቀቶች አሉ....» ብዬ እነሱንም አስረከብኹኝ::

«በቃ?...»

«ሞባይል፣ ገንዘብ፣ እስክሪብቶና ሳንቲሞች ናቸው የቀሩት...»

«አውጣቸው...»

ለካ ቁልፍም ይዣለሁ:: አረስቼው ነበር:: በሙሉ ተረከበኝ:: በዚሁ ወደ እስር ቤት ነው የምሄደው አልኹኝ ለራሴ::

«ጨረስኽ?...»

«አዎ..»

ፈተሸኝ:: የፊት፣ የኋላ፣ የደረት ኪሴን በሙሉ በጥንቃቄ ፈተሸ:: ሳንቲሞች ተገኙ:: እነሱም ተወሰዱ:: የዛሬውስ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጠብቋል::

«ጨርሻለሁ...»

መገናኛ የያዘው ፖሊስ ወደ ኮሚሽነሩ ቢሮ ይዞኝ ሄደ:: ፀሐፊያቸው ተቀበለችን::

«ቁጭ በሉ...» አለችን ብድግ ብላ::

ሶፋ ላይ ተቀመጥኹ::

«ከሰው ጋር ናቸው...» አለችው መገናኛ የያዘውን ፖሊስ::

ደቂቃዎች አለፉ:: ኮሚሽነሩን ለማነጋገር የመጡት «ከሰው ጋር ናቸው» እየተባሉ ተመለሱ::

ጠረጴዛ ላይ የተቀመጡ መፅሔቶችን ማገላበጥ ጀመርኹ:: ብዙዎቹ የፌዴራል ፖሊስ መፅሔቶች ናቸው:: አንዱ ለሚሊኒየም የወጣ ነው:: በውስጥ ገጾቹ «ዲሞክራሲ ስለሰፈነባት ኢትዮጵያ» እረጃጅም ሀተታዎች አስፍሯል:: ፈገግ ብዬ አልፎ... አልፎ አነበብኹት::

«አሁን መግባት ትችላላችሁ...» አለች ፀሐፊዋ፤ የአለቃዋን መመሪያ በስልክ ከተቀበለች በኋላ::

ሁላችንም ብድግ አልን:: መገናኛ የያዘው ፖሊስ ቀድሞኝ ኮሚሽነሩን ቢሮ ገባ:: ቢሮው ከጠበኹት በታች የጠበበ ነው:: በአእምሮዬ ግዙፍ ቢሮ ስዬ ነበር:: ምክትል ኮሚሽነሩ ተሽከርካሪ ወንበራቸው ላይ ጉብ ብለዋል:: ሲቪል ነው የለበሱት:: ኮስተር ብለዋል:: ፊት ለፊታቸው እረዳታቸው (የሕግ ባለሙያ ይመስሉኛል) ተቀምጠዋል:: እሳቸውም ሲቪል ነው የለበሱት::

«ቁጭ በል...» አሉ ኮሚሽነሩ በሩ ጎን ያለውን ጥቁር ቆዳ ሶፋ እያመለከቱ:: ቁጭ አልኹኝ:: አቤት ምቾት:: ይዞኝ ነው የሰመጠው::

መገናኛ የያዘው ፖሊስ በሩን ዘግቶ ወጣ:: ለትንሽ ሴኮንዶች ፀጥታ ሰፈነ::

«ለምን እንደተፈለግህ ታውቀዋለህ?» አሉኝ ኮሚሽነሩ ቆጣ .... ቆጣ እያሉ እንደ ድንገት::

ዓይኔን ከእሳቸው ወደ ረዳታቸው፤ ከረዳታቸው ወደ እሳቸው ወረወርኹት:: ምላሽ አልሰጠኋቸውም::

ኮሚሽነሩ ጠረጴዛ ላይ በርካታ ወረቀቶች ተቀምጠዋል:: የጄኔራል ፃድቃን ፎቶና የእንግሊዘኛ ፅሁፍ ይታየኛል:: አርእስቱ ጐላ ጐላ ብሎ ይነበባል:: ከሳምንት በፊት በኢትዮ ሚዲያ ላይ የወጣው መጣጥፌ ፕሪንት አውት ነው::

«በፅሁፎቼ ነው ብዬ ነው የምገምተው...» አልኳቸው፤ በአንገቴ ወደ ወረቀቶቹ እያመላከትኹኝ:: ኮሚሽነሩ ከላይ ያለውን ወረቀት ብድግ አደረጉት:: በስቴፕለር ተያይዟል:: ከስር "BEN ALI'S 'ADVISE' TO MELES ZENAWI" የሚለው ፅሁፌ ተቀምጧል::

«ጄኔራል ፃድቃን! ጄኔራል ፃድቃን! እያልኽ ትፅፋለህ...» ብለው አቋረጡ ኮሚሽነሩ::

ተናደዋል:: የፊታቸው ገፅታ ሲለዋወጥ ይታየኛል:: ዓረፍተነገሩን መጨረስ አልቻሉም:: «መንግሥት ደርሶበታል:: ግብፅና ቱኒዚያ እንደተነሳው ዓይነት ብጥብጥ ልትጭር እየጣርኽ ነው...» አሉኝ፤ የጄኔራል ፃድቃን ፎቶ ያለበትን ፅሁፌን እያወዛወዙ::

አሁንም መልስ አልሰጠኋቸውም::

«ጄኔራል ፃድቃን ይሄን ያህል የሚፃፍለት ምን ስለሆነ ነው?..»

ንዴታቸው እየጨመረ ሲሄድ ይታየኛል::

«እኮ! ምን ስለሆነ ነው ተጋኖ የሚፃፍለት?...»

መልስ አልሰጠኋቸውም፡ ኮሚሽነሩ ቀጠሉ:: ስለጄኔራሉ ገና አልጨረሱም::

(ሳምንት ይቀጥላል)